በኢትዮጵያ ገቢዎችና ጉምሩክ ባለስልጣን
ETHIOPIAN CUSTOMS AUTHORITHY
የአዲስ አበባ ቃሊቲ ጉምሩክ ቅ/ጽ/ቤት
ADDIS ABABA KALITY CUSTOMS BRANCH OFFICE
የውስጥ ማስታወሻ /INTER OFFICE MEMO/

ቁጥር: ስ/አ/ጽ/ቤት 140/08

ቀን: 19/07/08 ዓ.ም

ለ: ሁሉም የሥራ ሂደቶች
ገላን ተርሚናል ጉምሩክ ማስተባበሪያ ቅ/ጽ/ቤት
ጉምሩክ ጉዳዮች አቤቱታ አጣሪ ጽ/ቤት
አ/አ/ቃ/ጉ/ቅ/ጽ/ቤት፣

ከ: ስራ አስኪያጅ ጽ/ቤት
አ/አ/ቃ/ጉ/ቅ/ጽ/ቤት፣

የዋጋና ታሪፍ ምደባ አሠራርና ፕሮግራም ልማት ዳይሬክቶሬት በደብዳቤ ቁጥር **3.1.0/663/08** በቀን መጋቢት **13/2008** ዓ.ም. **ለአገር ውስጥ አምራች ኢንዱስትሪዎች የሚሰጠውን የታሪፍ ከለላ** ወጥነት ባለው አኳኋን መምራት እንዲቻል የጉምሩክ ታሪፍ ደንብ ሁለተኛ መደብ (ሀ) አጠቃቀም በተመለከተ መመሪያ ቁጥር 45/2008 ተግባራዊ እንዲደረግ ከገንዘብና ኢኮኖሚ ልማት ሚኒስቴር የተላከውን መመሪያ መላኩን እና መመሪያው ተፈርሞ ከወጣበት ከመጋቢት 08 ቀን 2008 ዓ.ም. ጀምሮ በሚቆጠር ከዘጠና ቀናት በኋላ ተፈፃሚ እንዲሆን በገለፀልን መሠረት ተግባራዊ እንዲደረግ እያሳሰብኩ፤ የደብዳቤውን እና የመመሪያውን ኮፒ 38 ገፅ በዚህ ሸኚ ደብዳቤ የተላከ መሆኑን እገልፃለሁ፡

ከሠላምታ ጋር

ግልባጭ:-

- ለም/ስራ አስኪያጅ /የጉምሩክ ጉዳዮች/
- ለም/ስራ አስኪያጅ /የሞደርናይዜሽን ኮርፖሬት ሥራዎች ዘርፍ/

አ.አ ቃሊቲ ጉምሩክ ቅ/ጽ/ቤት

ቁጥር 3/1.0/668/08
Ref. No
ቀን 13 መጋቢት 2008
Date

የጉምሩክ ሥነ-ሥርዓት ለሚፈፀምባቸው ቅ/ጽ/ቤቶች

በያሉበት

ጉዳዩ፡- የጉምሩክ ታሪፍ ደንብ ሁለተኛ መደብ (ሀ) አጠቃቀም መመሪያ ቁጥር 45/2008

መላኩን ይመለከታል፡፡

የገንዘብና ኢኮኖሚ ልማት ሚኒስቴር በቁጥር ገ/ኢ/1/2/93 በቀን 08/07/08 ዓ.ም በተፃፈ ደብዳቤ ለአገር ውስጥ አምራች ኢንዱስትሪዎች የሚሰጠውን የታሪፍ ከለላ ወጥነት ባለው አኳኋን መምራት እንዲቻል በማለት የጉምሩክ ታሪፍ ሁለተኛ መደብ (ሀ) አጠቃቀም መመሪያ መዘጋጀቱን ገልጾልናል፡፡

ስለሆነም የተላለፈው መመሪያ ተግባራዊ እንዲደረግ ከገንዘብና ኢኮኖሚ ልማት ሚኒስቴር የተላከውን የመመሪያውን 37 ገፅ አባሪ አድርገን የላክንላችሁ መሆኑን እየገለፅን፣ መመሪያው ተፈርሞ ከወጣበት ከመጋቢት 08 ቀን 2008 ዓ.ም. ጀምሮ በሚቆጠር ከዘጠና ቀናት በኋላ ተፈፃሚ እንዲሆን እናሳስባለን፡፡

ከሠላምታ ጋር

ግልባጭ

- ለክቡር ዋና ዳይሬክተር ጽ/ቤት
- ለጉምሩክ ፕሮግራም ልማትና ድጋፍ ሥራዎች ዘርፍ
- ለደንበኞች አገልግሎት ዳይሬክቶሬት
- ለጉምሩክ ቅ/ጽ/ቤቶች ድጋፍና ክትትል ዳይሬክቶሬት
- ለጉምሩክ ጉዳዮች አቤቱታ አጣሪ ጽ/ቤት
- ለህግ ምክር አስተያየት ቡድን
- ለታሪፍ ምደባ አ/ነ/ል/ቡድን

ኢትዮጵያ ገቢዎችና ጉምሩክ ባለሥልጣን

- ለባህርና ትራንዚት ሎጂስቲክስ አገልግሎት ድርጅት
- ለሞደርን ትራንዚተሮች ማህበር
- ለኢትዮጵያ ፍሬት ፎርዋርድስ ኤንድ ሽፒንግ ኤጀንትስ አሶስየሽን
- ለጉምሩክ አስተላላፊዎችና አሰሪዎች ማህበር

አዲስ አበባ

ኢትዮጵያ ፌደራላዊ ደሞክ...
145
12/7/08

773
12/07/08

በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ
የገንዘብና ኢኮኖሚ ትብብር ሚኒስቴር
The Federal Democratic Republic of Ethiopia
Ministry of Finance and Economic Cooperation

ቁጥር 7/ቌ/1/2/93
Ref.No
ቀን 8/7/2008
Date

ለኢትዮጵያ ገቢዎችና ጉምሩክ ባለሥልጣን
ለኢንዱስትሪ ሚኒስቴር
አዲስ አበባ

ለአገር ውስጥ አምራች ኢንዱስትሪዎች የሚሰጠውን የታሪፍ ከለላ ወጥነት ባለው አኳኋን መምራት እንዲቻል የጉምሩክ ታሪፍ ደንብ ሁለተኛ መደብ "ሀ" አጠቃቀም መመሪያ ተዘጋጅቷል።

ስለዚህ የመመሪያውን 35 ገጽ ከዚህ ጋር አባሪ በማድረግ የላክን ስለሆነ መመሪያው ተፈርሞ በወጣ በ90 ቀናት ውስጥ ተፈጻሚ እንዲደረግ እናሳስባለን።

ከሠላምታ ጋር

አብዱልአዚዝ መሐመድ
ሚኒስትር

ግልባጭ
- ለማክሮ ኢኮኖሚ ፖሊሲና ማኔጅመንት ዳይሬክቶሬት
- ለሕግ አገልግሎት ዳይሬክቶሬት
- ገንዘብና ኢኮኖሚ ትብብር ሚኒስቴር

Letter/Ser/TA

ስልክ
Tel 251-11-155 24 00,22 66 98
251-11-155 00 81,83 86 89
የፖ.ሣ.ቁ.
P.O.Box1905,1037
ፋክስ
Fax 251-11-156 01 24,55 14 96
251-11-155-11-38
አዲስ አበባ ኢትዮጵያ
Addis Ababa-Ethiopia

# የጉምሩክ ታሪፍ ደንብ ሁለተኛ

# መደብ (ሀ) አጠቃቀም

# መመሪያ ቁጥር 45/2008

መጋቢት 2008 ዓ.ም

የጉምሩክ ታሪፍ በገቢ ዕቃዎች ወይም በአንዳንድ የወጪ ዕቃዎች ላይ የሚጣል ሆኖ ዕቃዎቹ በሚገቡበት ወይም በሚወጡበት በር ላይ በዕቃዎች ክብደት፣ ብዛት፣ ይዘት፣ ዋጋ፣ ወዘተ ላይ ተመስርቶ የሚከፈል የቀረጥ ዓይነት በመሆኑ፣

በገቢ ዕቃዎች ላይ የሚጣለው የጉምሩክ ታሪፍ ለመንግሥት ገቢ ከማመንጨት ባሻገር ከውጭ የሚገቡ ዕቃዎች አገር ውስጥ ከሚመረቱ ዕቃዎች ጋር ያላቸውን ተወዳዳሪነት በመቀነስ አገር ውስጥ የሚመረቱ ዕቃዎች ገበያ እንዲያገኙ ማድረግ አስፈላጊ በመሆኑ፣

በአገሪቱ የኢኮኖሚ ዕድገትና የልማት እንቅስቃሴ ተበረታትተው አዳዲስ የተቋቋሙ ኢንዱስትሪዎች ከውጭ የሚገቡ ዕቃዎችን አገር ውስጥ እንዲያመርቱ (Import substitution) ለማበረታታት እና በኢኮኖሚና በማህበራዊ ረገድ ስትራቴጂያዊ የሆኑ አምራቾችን መደገፍ እንዲቻል በጉምሩክ ታሪፍ ሁለተኛ መደብ (ሀ) የሚሠጠውን ከለላ በግልጽ ለመተግበርና ለማስፈጸም የጉምሩክ ታሪፍ ሁለተኛ መደብ (ሀ) አጠቃቀም መመሪያ ማውጣት አስፈላጊ በመሆኑ፣

የገንዘብና ኢኮኖሚ ትብብር ሚኒስቴር በሚኒስትሮች ምክር ቤት የጉምሩክ ታሪፍ ደንብ ቁጥር 80/1995 በተሠጠው ሥልጣን መሠረት ይህንን መመሪያ አውጥቷል::

## ክፍል አንድ

## ጠቅላላ

1. አጭር ርዕስ፤

ይህ መመሪያ "የጉምሩክ ታሪፍ የሁለተኛ መደብ (ሀ) አጠቃቀምን ለመወሰን የወጣ መመሪያ ቁጥር 45/2008" ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል::

2. ትርጓሜ፤

ሀ/ "የበጀት አመት" ማለት በኢትዮጵያ ዘመን አቆጣጠር ከሐምሌ 1 እስከ ሚቀጥለው አመት ሰኔ 30 ያለው ጊዜ ነው::

ለ/ "የምርት ዘመን" ማለት የተጠቃሚነት ልዩ የምስክር ወረቀት ከተሰጠበት ቀን ጀምሮ ለቀጣዩ አንድ አመት ያለው ጊዜ ወይም የተጠቃሚነት የምስክር ወረቀት ከተሰጠበት ወደ ኋላ ያለው የአንድ አመት የሚቆጠር ጊዜ ነው::

ሐ/ "የምስክር ወረቀት" ማለት በዚህ መመሪያ የተመለከቱትን መመዘኛዎች አሟልተው ለሚቀርቡ አምራቾች በኢንዱስትሪ ሚኒስቴር የሚሰጥ የሁለተኛ መደብ (ሀ) የጉምሩክ ታሪፍ ተጠቃሚነት ማረጋገጫ ሰነድ ነው::

መ/ "ሚኒስቴር" ማለት የገንዘብና ኢኮኖሚ ትብብር ሚኒስቴር ነው::

ሠ/ "ባለስልጣን" ማለት የኢትዮጵያ ገቢዎችና ጉምሩክ ባለሥልጣን ነው::

ረ/ "የምስክር ወረቀት ሰጪ አካል" ማለት የኢንዱስትሪ ሚኒስቴር ወይም ሚኒስቴሩ የሚወክለው አካል ነው።።

ሰ/ "የጉምሩክ ታሪፍ ሁለተኛ መደብ (ሀ) ማለት የሚኒስትሮች ምክር ቤት የጉምሩክ ታሪፍ ደንብ አካል የሆነ በልዩ መብት ከቀረጥ ነፃ የሆኑ ወይም አነስተኛ ቀረጥ የሚከፈልባቸውን ዕቃዎች ዝርዝር የያዘ ሰንጠረዥ ነው::

ሸ/ "አምራች ድርጅት" ማለት በጉምሩክ ታሪፍ ሁለተኛ መደብ (ሀ) የተጠቀሱትን ግብአቶች በመጠቀም የሚያመርት ወይም የሚገጣጥም ድርጅት ማለት ነው::

ቀ/ "ከሽያጭ የተገኘ ገቢ" ማለት አምራች ድርጅቱ በበጀት ዓመቱ ውስጥ የሸጠው በገበያ ዋጋ ላይ የተመሠረተ የምርትና የተረፈ ምርት ጠቅላላ የሽያጭ ዋጋ ማለት ነው።።

በ/ "ጠቅላላ የምርት ዋጋ" ማለት አምራች ድርጅቱ የሸጠው ጠቅላላ የምርት ዋጋ፣ በዓመቱ መጀመሪያና መጨረሻ ላይ በመጋዘን በነበሩ ያስቀላቸውና በከፊል የተመረቱ ምርቶች የመጋዘን ክምችት ላይ በታየ ለውጥ (Inventory Change) ምክንያት የተከሰተ የዋጋ ለውጥ፣ ለሌሎች የተሰጠ የኢንዱስትሪ አገልግሎት ዋጋ፣ ተገዝተው ምንም ዓይነት የምርት ሂደት ሳይከናወንባቸው ተመልሰው የተሸጡ ዕቃዎች ዋጋና ከሌላ ምንጭ የተገኘ ገቢን እንዲሁም ጠቅላላ የምርት ዋጋና ታክስን የሚያጠቃልል ሲሆን፣ ድጎማን አይጨምርም።።

ተ/ "ተጨማሪ እሴት" ማለት የሠራተኛ ደመወዝ እና ጥቅማ ጥቅም፣ የወለድ ክፍያ፣ የእርጅና ቅናሽ ወጪ፣ የትርፍ እና የትርፍ ገቢ ግብር ድምር ውጤት ወይም ከሽያጭ ከተገኘ ገቢ ላይ ቀጥተኛ የሆኑ የምርት ወጪዎች እና ቀጥተኛ ያልሆኑ የምርት ወጪዎች ሲቀነሱ የሚገኘው ውጤት ነው።

ቸ/ "ቀጥተኛ የምርት ወጪዎች" ማለት የጥሬ ዕቃ፣ የነዳጅና እና ሌሎች ተመሳሳይ አቅርቦቶች ወጪን፣ በሌሎች የተሰጡ የኢንዱስትሪ አገልግሎቶች ወጪን፣ ተገዝተው ምንም ዓይነት የምርት ሂደት ሳይከናወንባቸው ተመልሰው የተሸጡ ዕቃዎች ወጪን እና ጥቅም ላይ የዋለ የኤሌክትሪክ ወጪን የሚያጠቃልል ሲሆን፣ የሠራተኛ ደመወዝ እና ጥቅማ ጥቅምን አይጨምርም።

ኀ/ "ቀጥተኛ ያልሆኑ የምርት ወጪዎች" ማለት ለሙያዊ አገልግሎት፣ ለፖስታ አገልግሎት፣ ለስልክ አገልግሎት፣ ለኢንሹራንስ፣ ለማስታወቂያ፣ በሌሎች ለተሰጠ የትራንስፖርት አገልግሎት እና ለኪራይ የተከፈለ ክፍያን የሚያጠቃልል ሲሆን፣ የወለድ ክፍያን፣ የእርጅና ቅናሽ ወጪን እና ታክስን አያጠቃልልም።

ነ/ "የተጨማሪ እሴት መጣኔ" ማለት ተጨማሪ እሴት ለጠቅላላ ከሽያጭ ለተገኘ ገቢ ተካፍሎ የሚገኘው ውጤት መቶኛ ነው። ይህም በመደመርም ሆነ በመቀነስ የሚገኘው ውጤት ተመሳሳይ ነው የሚሆነው።

ኘ/ "ግብዓት" ማለት በሀገር ውስጥ ወይም በውጭ ሀገር የተመረቱ፣ በምርት ዘመኑ በምርት ሂደት ውስጥ ጥቅም ላይ የዋሉ ወይም የሚውሉ ጥሬ ዕቃዎች፣ ክፍሎች፣ አካላት፣ መያዣዎች እና መጠቅለያዎች የሚያጠቃልል ነው።

አ/ "የሀገር ውስጥ ግብዓቶች ዋጋ" ማለት በሀገር ውስጥ የተመረቱ ግብአቶች የመግዣ ዋጋ፣ የማጓጓዣ ወጪ፣ ቀረጥና ታክሶችንና ለግብዓቶቹ ወጪ የተደረጉ ሌሎች ክፍያዎችን ያጠቃለለ ዋጋ ነው።

ከ/ "የውጭ ሀገር ግብዓቶች ዋጋ" ማለት በውጭ ሀገር የተመረቱ ሆነው በቀጥታ ከውጭ ሀገር ወይም ከሀገር ውስጥ የተገዙ ግብዓቶች የመግዣ ዋጋ፣ የማጓጓዣ ወጪ፣ ቀረጥና ታክሶችንና ለግብዓቶቹ ወጪ የተደረጉ ሌሎች ክፍያዎችን ያጠቃለለ ሲሆን ተመላሽ ቀረጥና ታክሶችን አያካተትም።

ወ/ "ከውጭ ተገዝተው የሚገቡ ጥሬ ዕቃዎች መጣኔ" ማለት የውጭ ሀገር ግብዓቶች ዋጋ ለምርት ግብአትነት በዋሉ የሀገር ውስጥ ግብዓቶች ዋጋ እና የውጭ ሀገር ግብዓቶች ዋጋ ድምር ሲካፈል የሚገኘው ውጤት በመቶኛ ነው።

ዘ/ "የጉምሩክ ታሪፍ አንደኛ መደብ" ማለት በዓለም የጉምሩኮች ኅብረት በየአምስት ዓመት ወቅታዊ የሚደረገውን የሀርሞናይዝድ ሲስተም ቨርሽን የዕቃዎች አመዳደብና አሰያምን መሠረት በማድረግ ከምዕራፍ 1 እስከ ምዕራፍ 97 ተመድበው ወደአገራችን በሚገቡ ዕቃዎች ላይ የታሪፍ መጣኔ በመጣል ተግባራዊ የሚደረግበት ሠነድ ነው።

ዠ/ "የጉምሩክ ሕግ ማለት" የጉምሩክ ሕግ 859/2006 ማለት ነው።

3. <u>የተፈፃሚነት ወሰን፤</u>

ይህ መመሪያ በጉምሩክ ታሪፍ ሁለተኛ መደብ (ሀ) መሰረት የተጠቃሚነት ምስክር ወረቀት አግኝቶ ከውጭ የሚገቡ ግብአቶችን በመጠቀም በሚያመርት አምራች ድርጅት ሁሉ ላይ ተፈፃሚ ይሆናል።

## ክፍል ሁለት

## የምስክር ወረቀት መስጠት፣ ማደስና ማሻሻል፤

4. **መስፈርቶችና የመስፈርቶቹ አጠቃቀም ቅደም ተከተል፣**

ሀ/ በጉምሩክ ታሪፍ ሁለተኛ መደብ (ሀ) ተጠቃሚ ለመሆን የሚውሉ መስፈርቶች በጉምሩክ ታሪፍ ሁለተኛ መደብ (ሀ) መጠቀም በማያስችሉ ሥራዎች ውስጥ ያልተካተተ፣ የተጨማሪ እሴት መጣኔ መስፈርት እና አስፈላጊ ሆኖ ሲገኝ የታሪፍ አንቀጽ ለውጥ ናቸው።

ለ/ ከላይ በንዑስ አንቀጽ ሀ የተጠቀሱት መስፈርቶች በቅደም ተከተል ተፈፃሚ ይሆናሉ።

5. **የጉምሩክ ታሪፍ ሁለተኛ መደብ (ሀ) ተጠቃሚ ለመሆን የማያስችሉ ሥራዎች፣**

የሚከተሉት ሥራዎች የጉምሩክ ታሪፍ ሁለተኛ መደብ (ሀ) ተጠቃሚ ለመሆን አያስችሉም፡-

ሀ/ በምርት ማጓጓዝ ወይም ክምችት ወቅት ምርቱን ባለበት ሁኔታ ለማቆየት የሚከናወኑ ተግባራት፣

ለ/ ዕቃዎችን የማጓጓዝ ሂደት ለማቀላጠፍ ሲባል የሚከናወኑ ተግባራት፣

ሐ/ ዕቃዎችን ለማሸግ ወይም ለሽያጭ ለማዘጋጀት ሲባል የሚከናወኑ ተግባራት፣

መ/ ዕቃዎችን በአየር የማናፈስ፤ የማስጣት፣ የማድረቅ፣ የማቀዝቀዝ፣ የተበላሹ ክፍሎችን የመቀየር፣ ማለስለሻ የመቀባት ወይም ዝገት የማስወገድ፣ ተፈጥሮአዊ ሁኔታዎች በዕቃው ላይ ጉዳት እንዳያደርሱ ቀለም የመቀባት፣ የማጠብ፣ የማጽዳት፣ የማበጠር፣ የመፈተግ፣ የመለየት፣የመመዘን፣የመሞከር፣ የመለካት፣ የማሸግ፣ እሽጐችን የመፍታት፣ መልሶ የማሸግ፣ የመከፋፈል፣ ምልክት የማድረግ፣ በውሃ ወይም በሌላ ፈሣሽ ነገር እንዳይበላሽ መጠበቅ፣ በጨው የመንከር፣ የመላጥ፣ የመከካት፣ የመውቃት እና የእንስሳት ዕርድ የመሳሰሉ ቀላል ሂደቶች ከንውን፣

ሠ/ ለማጓጓዝ ተብሎ ተበታትነው ወደ ሀገር ውስጥ የሚገቡ ዕቃዎችን መልሶ የመገጣጠም ሥራ፣

ረ/ የብርድ ልብስ፣ የአንሶላ፣ የፎጣ እና ሌሎች ብትን ጨርቆችን ከውጭ በማስገባት በመጠን መቁረጥ፣ መቀምቀም እና መከፈፍ፣

በታሪፍ አንቀጽ ለውጥ መስፈርት መሰረት ይገመግማል፡፡ በዚህ አንቀጽ መሰረት በጉምሩክ ታሪፍ ሁለተኛ መደብ (ሀ) የታሪፍ ማበረታቻ ተጠቃሚ ለመሆን፦

ሀ/ የታሪፍ አንቀጽ ለውጥ ለማምጣት የምርት ሂደት ተከናውኖባቸው በመጨረሻ የሚገኘውን ምርት የሚያስገኙ ወደ ሀገር ውስጥ የሚገቡ ግብዓቶች የሚመደቡበት የታሪፍ አንቀጽ በመጨረሻ የሚገኘው የምርት ውጤት ከሚመደብበት የታሪፍ አንቀጽ በተለየ የታሪፍ አንቀጽ ላይ የሚመደቡ መሆን አለባቸው፡፡

ለ/ የምርት ሂደት ተከናውኖባቸው በመጨረሻ የሚገኘውን ምርት ከሚያስገኙ ግብዓቶች ውስጥ አንዳቸው እንኳን በመጨረሻ የሚገኘው የምርት ውጤት በሚመደብበት የታሪፍ አንቀጽ ላይ የሚመደቡ ከሆነ የታሪፍ አንቀጽ ለውጥ እንደተደረገ ስለማይቆጠር የታሪፍ ማበረታቻው ተጠቃሚ መሆን አያስችልም፡፡

ሐ/ ፈቃድ ሰጪው አካል በታሪፍ አንቀጽ ለውጥ መስፈርት መሰረት የጉምሩክ ታሪፍ ሁለተኛ መደብ ጥያቄዎችን ለመገምገም የምርቶችንና የግብዓቶችን የታሪፍ አመዳደብ በተመለከተ የባለሥልጣኑን መስሪያ ቤት የሙያ እገዛ ሊጠይቅ ይችላል፣

መ/ የባለሥልጣን መስሪያ ቤቱም በፈቃድ ሰጪው አካል የምርቶቹንና የግብዓቶቹን የታሪፍ አመዳደብ በተመለከተ የሙያ እገዛ ሲጠየቅ ፈጣን ምላሽ የመስጠት ግዴታ አለበት፣

8. <u>የምስክር ወረቀት ለማግኘት መቅረብ ያለባቸው ሰነዶች፤</u>

አምራች ድርጅት በጉምሩክ ታሪፍ ሁለተኛ መደብ (ሀ) የታሪፍ ማበረታቻ ተጠቃሚ ለመሆንና የምስክር ወረቀት ለማግኘት ለምስክር ወረቀት ሰጪ አካል ጥያቄ ሲያቀርብ የሚከተሉትን ሰነዶች ማቅረብ ይኖርበታል፡፡

ሀ/ ከዚህ መመሪያ ጋር በተያያዘው ቅጽ አንድ መሰረት በአምራች ድርጅቱ ተሞልቶና ተፈርሞ የቀረበ ማመልከቻ፣

ለ/ ለነባር አምራች ድርጅት ለበጀት አመቱ የታደሰ የንግድ ፈቃድ፣ ለአዲስ አምራች ድርጅት ለመጀመሪያው ዓመት ብቻ የኢንቨስትመንት ፈቃድ፣

ሐ/ ከዚህ መመሪያ ጋር በተያያዘው ቅጽ አራት /ሀ/ እና /ለ/ መሰረት በምርት ዘመኑ የድርጅቱን የማምረት አቅም፣ የምርት ዕቅድ እና የግብአት ፍላጐት ዕቅድ፣

መ/ ከዚህ መመሪያ ጋር በተያያዘው ቅጽ ሁለት መሰረት የድርጅቱን አጠቃላይ መግለጫ፣

ሠ/ ለነባር አምራች ድርጅት ከዚህ መመሪያ ጋር በተያያዘው ቅጽ ሦስት /ሀ/ እና /ለ/ መሰረት ያለፉት ሁለት የምርት ዘመናት የግብዓት አጠቃቀም፣ የምርት መጠን እና የሽያጭ አፈፃፀም ፣ አዲስ አምራች ድርጅት ከሆነ ይህን ማሟላት አይጠበቅበትም፡፡

ረ/ ከዚህ መመሪያ ጋር በተያያዘው ቅጽ አራት /ለ/ መሰረት አንድ ነጠላ /single unit/ ምርት ለማምረት ጥቅም ላይ የዋለው ወይም የሚውል የግብዓት-ምርት ጥምርታ እና የብክነት መጠን፣

ሰ/ የጉምሩክ ታሪፍ ሁለተኛ መደብ (ሀ) ተጠቃሚነት የምስክር ወረቀት አሰጣጥን በተመለከተ በዚህ መመሪያ ላይ በመመስረት የኢንዱስትሪ ሚኒስቴር ዝርዝር መመሪያ ሊያወጣ ይችላል፡፡

9. <u>በአመልካቹ የሚቀርብ መረጃን ስለማረጋገጥ፤</u>

ሀ/ የምስክር ወረቀት ሰጪው አካል የጉምሩክ ታሪፍ የሁለተኛ መደብ (ሀ) ተጠቃሚ ለመሆን በአመልካች የሚቀርቡ መረጃዎችን ትክክለኛነት አስፈላጊውን ግምገማ በማካሄድ ያረጋግጣል፤ አስፈላጊ ሆኖ ሲገኝ የመረጃውን ትክክለኛነት የውጪ ኦዲተሮች የኦዲት ሪፖርት መጠቀም ይችላል፡፡

ለ/ የውጭ ኦዲተሮች የኦዲት ሪፖርት የሂሳብ ሚዛንና የኪሳራና ትርፍ መግለጫዎችን ብቻ ሳይሆን የተጨማሪ እሴት መግለጫዎችንም ያካተቱ መሆን ይኖርባቸዋል፡፡

ሐ/ የምስክር ወረቀት ሰጪው አካል በሚያደርገው ማጣራት በአመልካቹ የቀረበው መረጃ ወይም በውጭ ኦዲተሮች ሪፖርት ላይ ስህተት ያለበት መሆኑን ከደረሰበት ይህንኑ ለአመልካቹ በማሳወቅ ተገቢውን ማስተካከያ እንዲያደርግ ሊጠይቅ ይችላል፡፡

መ/ አመልካቹ ባቀረበው መረጃ ወይም በውጭ ኦዲተሮች ሪፖርት መሰረት በጉምሩክ ታሪፍ የሁለተኛ መደብ (ሀ) ተስተናግዶ ከሆነ እና በኋላ ላይ ቀርቦ የነበረው መረጃ ሀሰት ሆኖ ከተገኘ በአመልካቹ እና በኦዲተሩ ላይ አስፈላጊው ህጋዊ እርምጃ ሊወሰድ ይችላል፡፡

10. <u>የምስክር ወረቀት ስለማሳደስ፤</u>

ተጠቃሚዎች የምስክር ወረቀቱን ለማሳደስ የምርት ዘመኑ ባበቃ በአንድ ወር ጊዜ ውስጥ የሚከተሉትን ቅድመ ሁኔታዎች ማሟላት ይጠበቅባቸዋል፡-

ሀ/ ከዚህ መመሪያ ጋር በተያያዘው ቅጽ አምስት መሰረት የዕድሳት ማመልከቻ፣

ለ/ ለበጀት አመቱ የታደሰ የንግድ ፈቃድ፣

ሐ/ ከዚህ መመሪያ ጋር በተያያዘው ቅጽ አራት /ሀ/ እና /ለ/ መሰረት በምርት ዘመኑ የድርጅቱን የማምረት አቅም፣ የምርት ዕቅድ እና የግብአት ፍላጐት ዕቅድ፣

መ/ ከዚህ መመሪያ ጋር በተያያዘው ቅጽ ሁለት መሰረት የድርጅቱ አጠቃላይ መግለጫ፣

ሠ/ ከዚህ መመሪያ ጋር በተያያዘው ቅጽ ሦስት /ሀ/ እና /ለ/ መሰረት ያለፉት ሁለት የምርት ዘመናት የግብዓት አጠቃቀም፣ የምርት መጠን እና የሽያጭ አፈፃፀም ፣ ሁለት ዓመት ያልሞላው ከሆነ አንድ ምርት ዘመን የግብዓት አጠቃቀም፣ የምርት መጠን እና የሽያጭ አፈፃፀም፣

ረ/ ከዚህ መመሪያ ጋር በተያያዘው ቅጽ አራት /ለ/ መሰረት አንድ ነጠላ /single unit/ ምርት ለማምረት ጥቅም ላይ የዋለ ወይም የሚውል የግብዓት - ምርት ጥምርታ እና የብክነት መጠን፣

ሰ/ የምስክር ወረቀቱ ሳይታደስ የምርት ዘመኑ ያለፈ ከሆነ የጉምሩክ ታሪፍ ሁለተኛ መደብ (ሀ) ተጠቃሚነት መብት ለጊዜው ሊነሳ ይችላል።

11. <u>የምስክር ወረቀት ስለማሻሻል፤</u>

ሀ/ የምስክር ወረቀት ሊሻሻል የሚችለው፡-

1. የተጠቃሚው ድርጅት ስም፣ አድራሻ፣ የድርጅት ባለቤት ለውጥ ሲኖር፣
2. የግብዓት-ምርት ጥመርታ ለውጥ ሲኖር፣
3. የማምረት አቅም ለውጥ ሲኖር፣
4. የብክነት መጠን ለውጥ ሲኖር፤ ወይም
5. በተለየ ምክንያት የምስክር ወረቀት ሰጪው አካል የምስክር ወረቀቱ መሻሻል ያለበት እንደሆነ ሲያምን ነው።

ለ/ የምስክር ወረቀቱን ለማሻሻል የሚከተሉት ሰነዶች መቅረብ አለባቸው፤

1. ከዚህ መመሪያ ጋር በተያያዘው ቅጽ ስድስት መሰረት የዕድሳት ማመልከቻ፣
2. ለበጀት አመቱ የታደሰ የንግድ ፈቃድ፣
3. ከዚህ መመሪያ ጋር በተያያዘው ቅጽ አራት /ሀ/ እና /ለ/ መሰረት በምርት ዘመኑ የድርጅቱን የማምረት አቅም፣ የምርት ዕቅድ እና የግብአት ፍላጎት ዕቅድ፣
4. ከዚህ መመሪያ ጋር በተያያዘው ቅጽ ሁለት መሰረት የድርጅቱ አጠቃላይ መግለጫ ፣
5. ከዚህ መመሪያ ጋር በተያያዘው ቅጽ አራት /ለ/ መሰረት አንድ ነጠላ /single unit/ ምርት ለማምረት ጥቅም ላይ የዋለ ወይም የሚውል የግብዓት-ምርት ጥመርታ እና የብክነት መጠን፣

12. <u>የምስክር ወረቀት ስለሚሰረዝበት ወይም ስለሚታገድበት ሁኔታ፤</u>

ሀ/ በተጠቃሚዎች በሚቀርብ ጥያቄ መሰረት የጉምሩክ ታሪፍ ሁለተኛ መደብ (ሀ) ተጠቃሚነት የምስክር ወረቀት ሊሰረዝ ይችላል፡፡

ለ/ ማናቸውም የምስክር ወረቀት የይሰረዝልኝ ጥያቄ በጽሑፍ መቅረብ ያለበት ሲሆን በጉምሩክ ታሪፍ ሁለተኛ መደብ (ሀ) ተጠቃሚነት መብት መሰረት ወደ አገር ውስጥ የገባው ግብአት ተጠቃሎ ጥቅም ላይ የሚውልበትን ጊዜ መግለፅ አለበት፡፡ ሆኖም ጥቅም ላይ ሳይውል በቀረው ግብዓት በጉምሩክ ታሪፍ አንደኛ መደብ መሰረት ቀረጥ ይከፈልበታል፡፡

ሐ/ የዚህ አንቀፅ ንዑስ አንቀጽ (ለ) እንደተጠበቀ ሆኖ ወደ አገር የገቡ ግብዓቶች በጉምሩክ ታሪፍ ሁለተኛ መደብ (ሀ) ለመጠቀም የሚያስችል የምስክር ወረቀት ለተሰጠው እና ግብአቱን በተቀመጡት መስፈርቶች መሰረት ለሚጠቀም አምራች መተላለፋቸው ከተረጋገጠ በጉምሩክ ታሪፍ አንደኛ መደብ መሰረት ቀረጥ እንዲከፍሉ ሳይጠየቅ የምስክር ወረቀቱ ሊሰረዝ ይችላል፡፡

መ/ የተሳሳቱ መረጃዎችን በማቅረብ የተገኘ የጉምሩክ ታሪፍ ሁለተኛ መደብ (ሀ) የተጠቃሚነት የምስክር ወረቀት በማናቸውም ጊዜ ሊታገድ ወይም ሊሰረዝ ይችላል፡፡

ሠ/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ /መ/ መሰረት የምስክር ወረቀት ሰጪው አካል የሚወስዳቸውን እርምጃዎች ለባለስልጣኑ መስሪያ ቤት ወዲያውኑ በደብዳቤ ያስታውቃል፡፡

ረ/ የምስክር ወረቀት ሰጪውን አካል በማሳሳት ሆን ተብሎ አለአግባብ ጥቅም ለማግኘት ሲባል የተገኘ የጉምሩክ ታሪፍ ሁለተኛ መደብ (ሀ) የተጠቃሚነት የምስክር ወረቀት በጉምሩክ ሕግ ማስጠየቁ እንደተጠበቀ ሆኖ የምስክር ወረቀቱ ሊሰረዝ ወይም ሊታገድ ይችላል። እንዲሁም አለአግባብ በጉምሩክ ታሪፍ ሁለተኛ መደብ (ሀ) መሰረት የገባው ዕቃ በጉምሩክ ታሪፍ አንደኛ መደብ መሰረት ቀረጥ እንዲከፈልበት ይደረጋል።

ሰ/ የባለሥልጣን መስሪያ ቤቱ የምስክር ወረቀቱ እንዲታገድ ወይም እንዲሰረዝ የሚያደርጉ ጥፋቶችን ፈጽመዋል ብሎ ያመነባቸውን የጉምሩክ ታሪፍ ሁለተኛ መደብ (ሀ) ተጠቃሚ አምራች ድርጅቶችን ዝርዝር ተገቢው እርምጃ እንዲወሰድ በየጊዜው ለፈቃድ ሰጪው አካል ማስተላለፍ አለበት።

## ክፍል ሦስት

## ግብዓቶች ስለመጠቀምና መረጃ ስለመያዝ

13. <u>የግብአት መጠንና አጠቃቀም፤</u>

ሀ/ የማንኛውም የጉምሩክ ታሪፍ ሁለተኛ መደብ (ሀ) ተጠቃሚ የሆነ አምራች ድርጅት የግብአት አጠቃቀም በቅጽ አራት /ሀ/ እና /ለ/ ላይ ለምርት ዘመኑ በተያዘው ዕቅድ መሰረት መሆን አለበት።

ለ/ የግብአት አጠቃቀሙ በቅጽ አራት /ለ/ በተመለከተው የግብአት ምርት ጥመርታና የብክነት መጠን ልክ መሆን አለበት።

ሐ/ ማንኛውም የጉምሩክ ታሪፍ ሁለተኛ መደብ (ሀ) ተጠቃሚ የሆነ አምራች በሁለተኛ መደብ (ሀ) ያስገባውን ግብዓት የምስክር ወረቀት ሰጪው አካል ሳያውቀው በተጠቃሚነት የምስክር ወረቀት ላይ ከተጠቀሰው የምርት አይነት ውጭ ለሌላ ተግባር ማዋል አይችልም።

መ/ አምራች ድርጅቱ በምርት ዘመኑ ካስመዘገበው የማምረት አቅም በላይ የማምረት አቅሙ ቢጨምር ወይም የማምረት ዕቅዱን ማሻሻል ቢፈልግ ለምስክር ወረቀት ሰጪው አካል በቅጽ ስድስት መሰረት ማመልከት አለበት።

14. <u>የግብዓት ምርት ጥመርታ መጠን ስለማጸደቅ፤</u>

የግብዓት ምርት ጥመርታ መጠን በአምራች ድርጅቱ በቅጽ አራት /ለ/ መሰረት ተሞልቶ ሲቀርብ ትክክለኛነቱ ተጣርቶ በምስክር ወረቀት ሰጪው አካል ተቀባይነት ሲያገኝ ይጸድቃል::

15. <u>በምርት ሂደት ስለሚደርስ የግብአት ብክነት፤</u>

የምስክር ወረቀት ሰጪው አካል አገራዊ የግብዓት-ምርት ጥመርታ (Standard input output coefficient) ለተዘጋጀላቸው የኢንዱስትሪ ዘርፎች አምራቹ በሚያቀርበው ጥያቄ መሰረት የምርቱን ባህሪና ሁኔታ ከግምት ውስጥ በማስገባትየግብአት ብክነት መጠን ወስኖ ይፈቅዳል።

16. <u>በጉምሩክ ታሪፍ ሁለተኛ መደብ (ሀ) ተጠቃሚዎች የሚያዝ መረጃ፤</u>

ሀ/ በጉምሩክ ታሪፍ ሁለተኛ መደብ (ሀ) ተጠቃሚ የሆነ ማንኛውም አምራች ድርጅት የሚከተሉትን መረጃዎች መዝግቦ መያዝ አለበት።

1. የሁለተኛ መደብ (ሀ) ተጠቃሚ በሆነበት ጊዜ ወደ አገር ውስጥ ያስገባውን የግብአት መጠን በየምርት ዘመኑ፣
2. በምርት ዘመኑ ከአገር ውስጥ የገዛውን የሀገር ውስጥ ግብአት መጠን፣ እንዲሁም ከሌሎች አስመጪዎች በግዥም ሆነ በሌላ መልኩ ያገኘውን የውጭ ግብአት መጠን፣
3. በምርት ዘመኑ የተመረተውን የምርት አይነት፣ የምርት መጠን እና ዋጋ፣
4. በምርት ዘመኑ ያጋጠመ የብክነት መጠን፣

ለ/ ማምረት ከጀመረ ከስድስት ወር በታች የሆነ አዲስ አምራች ድርጅት መረጃዎቹን በቀጣይ በጀት ዓመት አጠቃሎ ያቀርባል።

ሐ/ የተጠቃሚነት የምስክር ወረቀት የተሰጠው አምራች ድርጅት ከዚህ መመሪያ ጋር በተያያዙት ቅጽ ሰባት /ሀ/ እና /ለ/ መሰረት የምርትና የግብዓት መረጃዎችን ሞልቶ የምርት ዘመኑ በተጠናቀቀ በሰላሳ ቀን ውስጥ ማቅረብ አለበት፣

መ/ የተጠቃሚነት የምስክር ወረቀት የተሰጠው አምራች ድርጅት ማንኛውንም በጉምሩክ ታሪፍ ሁለተኛ መደብ (ሀ) ተጠቃሚነት ምክንያት የሚይዛቸውን መረጃዎች እስከ 5 የምርት ዘመን ድረስ በማቆየት በባለስልጣን መስሪያ ቤት ወይም በሚኒስቴር መ/ቤት ወይም በምስክር ሰጪ አካል ሲጠየቅ የማቅረብ ግዴታ አለበት፡፡

## ክፍል አራት

## የምስክር ወረቀት ሰጪ አካል እና የባለሥልጣኑ መሥሪያ ቤት ተግባርና ኃላፊነት፤

### 17. የምስክር ወረቀት ሰጪ አካል፣

ሀ/ የምስክር ወረቀት ሰጪ አካል አምራች ኢንዱስትሪዎች በጉምሩክ ታሪፍ ሁለተኛ መደብ (ሀ) የታሪፍ ማበረታቻ ተጠቃሚ ለመሆን ጥያቄ ሲያቀርቡ በዚህ መመሪያ የተዘረዘሩት መስፈርቶችና ቅድመ ሁኔታዎች መሟላታቸውን በማረጋገጥ የጉምሩክ ታሪፍ ሁለተኛ መደብ (ሀ) ተጠቃሚነት የምስክር ወረቀት ይሰጣል፡፡

ለ/ የጉምሩክ ታሪፍ ሁለተኛ መደብ (ሀ) ተጠቃሚዎች ማሟላት ያለባቸው መስፈርቶች፣ ግዴታዎችና ቅድመ ሁኔታዎች በሚሰጣቸው የምስክር ወረቀት ጀርባ ላይ ይገለጻል፡፡

ሐ/ የሚሰጠው የምስክር ወረቀት የሚያገለግለው ለሦስት ዓመታት ሆኖ በዚህ መመሪያ በተደነገገው መሠረት በየዓመቱ የሚታደስ ይሆናል፡፡

### 18. የባለሥልጣን መስሪያ ቤቱ ተግባርና ኃላፊነት

የባለሥልጣን መ/ቤቱ በዚህ መመሪያ መሠረት የሚከተሉት ተግባርና ኃላፊነቶች ይኖሩታል፤

ሀ/ የተጠቃሚነት የምስክር ወረቀት የተሰጠው አምራች ድርጅት ጥሬ ዕቃዎችን ወደ አገር በሚያስገባበት ወቅት የምስክር ወረቀቱን ፎቶ ኮፒ ከዲክላራሲዮን ጋር አያይዞ እንዲያቀርብ ያደርጋል፤

ለ/ አምራቹ በወቅቱ የታደሰ የጉምሩክ ታሪፍ ሁለተኛ መደብ (ሀ) ተጠቃሚነትን የሚያሳይ የምስክር ወረቀት ሲያቀርብ በሁለተኛ መደብ (ሀ) መሰረት እንዲስተናገድ ያደርጋል፤

ሐ/ በምስክር ወረቀቱ ላይ የተገለጸው እያንዳንዱ የግብአት አይነት እና የታሪፍ ቁጥር በዲክላራሲዮኑ ላይ ከተገለጸው ጋር አንድ አይነት መሆኑን ያረጋግጣል፤

መ/ አባሪ ሰነዶችንና የዲክላራሲዮን ቅጂዎችን እንዲሁም አስፈላጊ የሆኑ ሰነዶችን በየተጠቃሚዎች ለይቶ ፋይል አድርጎ ይይዛል፤

ሠ/ እንደአስፈላጊነቱ በየፋብሪካዎቹ በአካል በመገኘት በሚሰበስበው መረጃ መሰረት የእያንዳንዱን የጉምሩክ ታሪፍ የሁለተኛ መደብ (ሀ) ተጠቃሚ የምርትና የግብዓት አጠቃቀም አመታዊ ሪፖርት በቅጽ ስምንት መሰረት ያዘጋጃል፤ እንደአስፈላጊነቱ ለሚኒስቴሩና ለምስክር ወረቀት ሰጪ አካል ያቀርባል።

ረ/ በጉምሩክ ታሪፍ ሁለተኛ መደብ (ሀ) መሰረት የተስተናገዱ የመብቱ ተጠቃሚ ዕቃዎች ከጉምሩክ ክልል ከወጡ በኋላ በመብቱ በትክክል መጠቀማቸውን ለማረጋገጥ እንደአስፈላጊነቱ የድህረ ዕቃ አወጣጥ ኦዲት ሊያደርግ ይችላል።

ሰ/ ከላይ የተዘረዘሩትን ተግባርና ኃላፊነት ለማስፈጸም የሚያስችለውን ዝርዝር መመሪያ የባለስልጣን መስሪያ ቤቱ ሊያወጣ ይችላል።

## ክፍል አምስት

## ልዩ ልዩ ድንጋጌዎች

### 19. የመስፈርቶች ክለሳ ስለማድረግ፤

የተጨማሪ እሴት መጣኔ እና ሌሎች ለጉምሩክ ታሪፍ ሁለተኛ መደብ ተጠቃሚነት የተቀመጡ መስፈርቶች የአምራች ኢንዱስትሪዎችን የርስ በርስ ትስስር በሚያጠናክር መልኩ በየሦስት ዓመቱ ክለሳ ይደረግባቸዋል።

### 20. የአገልግሎት ክፍያ፤

ማናቸውም የጉምሩክ ታሪፍ ሁለተኛ መደብ (ሀ) ተጠቃሚ የሆነ አምራች ድርጅት የምስክር ወረቀት በማግኘት፣ በማሳደስ እና በማሻሻል ረገድ ለሚያገኘው አገልግሎት በመንግስት በሚወሰነው የማስከፈያ ልክ መሰረት የአገልግሎት ክፍያ ይከፍላል።

21. <u>ጥፋቶች እና ቅጣቶች፤</u>

በዚህ መመሪያ ከተቀመጠው አሠራር ውጭ አለአግባብ ጥቅም ለማግኘት በማሰብ ግብአቶችን ወደ ሀገር ያስገባ እና የተጠቀመ አምራች ድርጅት አግባብነት ባለው የጉምሩክ ሕግ መሰረት ተጠያቂ ይሆናል፡፡

22. <u>ቅሬታ እና አቤቱታ፤</u>

በፈቃድ ሰጪው አካል ወይም በባለስልጣኑ ውሳኔና አገልግሎት አሰጣጥ ላይ ቅሬታ ያለው የጉምሩክ ታሪፍ ሁለተኛ መደብ (ሀ) ተጠቃሚ አምራች ድርጅት ቅሬታውንና አቤቱታውን እንደሚከተለው ማቅረብ ይችላል፡፡

ሀ/ በባለስልጣኑ መስሪያ ቤት ውሳኔና አገልግሎት አሰጣጥ ላይ የሚቀርቡ ቅሬታዎችና አቤቱታዎች በጉምሩክ አዋጅ 859/2007 በተደነገገው መሰረት ይታያሉ፡፡

ለ/ በፈቃድ ሰጪው አካል ውሳኔና አገልግሎት አሰጣጥ ላይ የሚቀርቡ ቅሬታዎችና አቤቱታዎች ለፈቃድ ሰጪው አካል ከቀረቡ በኋላ፣ በፈቃድ ሰጪው አካል በኩል ለሚኒስቴሩ መስሪያ ቤት ቀርበው በታሪፍ ኮሚቴ ይታያሉ፡፡

23. <u>ፈቃድ የተሰጣቸውን የአምራች ድርጅቶች እና የተሰረዙ ፈቃዶችን ዝርዝር ስለማሳወቅ፤</u>

የምስክር ወረቀት ሰጪው አካል ፈቃድ የሰጣቸውን አምራች ድርጅቶች ዝርዝር፣ የተረጋገጠ የምስክር ወረቀት ኮፒ እና ሌሎች አባሪ ሰነዶችን ግልባጭ ለባለሥልጣን መ/ቤቱ እና ለሚመለከታቸው አካላት ያሰራጫል፡፡

24. <u>መመሪያውን ስለማሻሻል፤</u>

ይህ መመሪያ እንደ አስፈላጊነቱ በማንኛውም ጊዜ በሚኒስቴሩ ሊሻሻል ይችላል፡፡

25. <u>የመሸጋገሪያ ድንጋጌ፤</u>

ሀ/ ይህ መመሪያ ሥራ ላይ ከመዋሉ በፊት የተስተናገዱ የጉምሩክ ታሪፍ ሁለተኛ መደብ (ሀ) ተጠቃሚዎች እና ከዚሁ ጋር በተያያዘ በአንግልጥል ላይ ያሉ ጉዳዮች ሁሉ በዚህ መመሪያ የተደነገገዉን እንዳሚሉ ይቀጠራል፡፡

ለ/ ማንኛዉም ነባር የጉምሩክ ታሪፍ ሁለተኛ መደብ (ሀ) ተጠቃሚ አምራች ድርጅት ይህ መመሪያ ተፈርሞ ከወጣበት ቀን ጀምሮ ባሉት ዘጠና ቀናት ዉስጥ በመመሪያዉ መሰረት አስፈላጊ የሆኑትን ቅድመ ሁኔታዎች በማሟላት የተጠቃሚነት የምስክር ወረቀት በማግኘት ለባለስልጣን መስሪያ ቤቱ ማቅረብ አለበት፡፡

ሐ/ አንድ የሁለተኛ መደብ (ሀ) ተጠቃሚ አምራች ድርጅት በዚህ አንቀጽ በፊደል ተራ (ለ) በተቀመጠው የጊዜ ገደብ ውስጥ የምስክር ወረቀቱን አሟልቶ ካላቀረበ በአንደኛ መደብ የጉምሩክ ታሪፍ መሠረት ቀረጥና ታክሱን እንዲከፍል ይደረጋል፡፡

26. <u>የተሻሩ መመሪያዎች፤</u>

ሀ/ በጉምሩክ ታሪፍ ሁለተኛ መደብ (ሀ) መሠረት አምራቾች የሚያስገቧቸዉን ግብአቶች አጠቃቀም ለመቆጣጠር የወጣ መመሪያ ቁጥር 35/2005፣

ለ/ የጉምሩክ ታሪፍ ሁለተኛ መደብ (ሀ) አጠቃቀምን በተመለከተ በቁጥር 3/21/429 ጥር 5 ቀን 1997 ከገንዘብና ኢኮኖሚ ልማት ሚኒስቴር የተላለፈ መመሪያ፣

ሐ/ የገንዘብና ኢኮኖሚ ልማት ሚኒስቴር በቁጥር ማኢ-30/47/70 በ16/11/2005 ባስተላለፈዉ የታሪፍ ማሻሻያ መሰረት ከቆዳ ኢንዱስትሪ ልማት ኢንስቲትዩት በቁጥር 02.1.8.6/31-9 በ24/11/05 የተላለፈው የቆዳ አምራቾች ዝርዝር፣

መ/ በቁጥር ማኢ-30/47/56 በ04/08/05 የተላለፈን የጉምሩክ ታሪፍ ማሻሻያ አፈጻጸምን በተመለከተ ከጨርቃጨርቅ ኢንዱስትሪ ልማት ኢንስቲትዩት በቁጥር 02.1.6/187 ሚያዝያ 15 ቀን 2005 ዓ.ም. የተላለፈ መመሪያ እና

ሠ/ እነዚህን መመሪያዎች ለማስፈጸም በባለሥልጣን መሥሪያ ቤቱና በሚመለከታቸው ሁሉ የተላለፉ መመሪያዎች እንዲሁም ልማዳዊ አሠራሮች ይህ መመሪያ ሥራ ላይ ከዋለበት ቀን ጀምሮ የተሻሩ ናቸው፡፡

27. <u>መመሪያው የሚፀናበት ጊዜ፤</u>

ይህ መመሪያ ተፈርሞ ከወጣበት ቀን ጀምሮ በሚቆጠር ከዘጠና ቀናት በኋላ የፀና ይሆናል፡፡

አብዱልአዚዝ መሐመድ
የገንዘብና ኢኮኖሚ ትብብር
ሚኒስትር

## ቅጽ አንድ

# የሁለተኛ መደብ ተጠቃሚ ለመሆን የቀረበ ማመልከቻ

እኔ ........................................................የማምረት ሥራ መስክ የተሰማራሁ የጉምሩክ ታሪፍ ሁለተኛ መደብ "ሀ" ተጠቃሚ መሆን እችል ዘንድ ከዚህ ማመልከቻ ጋር አያይዤ ባቀረብኳቸው መረጃዎች መሰረት የጉምሩክ ታሪፍ ሁለተኛ መደብ "ሀ" የተጠቃሚነት የምስክር ወረቀት እንዲሰጠኝ አመለክታለሁ፡፡

ማረጋገጫ

1. የተሰጠው መብት በትክክል ሥራ ላይ መዋሉን የሚኒሰቴር መስሪያ ቤቱና የባለስልጣን መስሪያ ቤቱ ለሚያደርጉት አስፈላጊውን ትብብር ለማድረግ፣
2. የቀረበው የምርት ግብዓት ፍላጎት በምርት ዕቅድ መሰረት መሆኑን፣
3. የጉምሩክ ታሪፍ ሁለተኛ መደብ ተጠቃሚ ለመሆን የተቀመጡትን ግዴታዎች በሙሉ ሳሟላ፣

ማረጋገጫ ስጥቻለሁ፡፡

የአመልካች ስም............................................................

የድርጅቱ ስም..............................................................

የግብር ከፋይ መለያ ቁጥር................................................

ማመልከቻ ቀረበበት ቀን....................................................

የአባሪ ገጽ ብዛት...........................................................

ፊርማ.........................................................................

የድርጅቱ ማህተም...........................................................

# ቅጽ ሁለት

## የድርጅቱ አጠቃላይ መግለጫ

1. ድረጅቱ የተቋቋመበት ዘመን..........................................................................
2. የድርጅቱ ካፒታል መጠን፦

   ሀ. ቋሚ የማምረቻ መሣሪያዎች በብር..................................................

   ለ. ሕንጻ በብር..........................................................................

   ሐ. የሥራ ማስኬጃ በብር ..........................................................

   መ. ሌሎች በብር..........................................................................

3. የድርጅቱ ሠራተኞች ብዛት፦
   ሀ. ቋሚ ሠራተኞች..........................................................
   ለ. ጊዜያዊ ሠራተኞች ..........................................................
   ሐ. ሌሎች ..........................................................................
4. የድርጅቱ የይዞታ ሁኔታ፦

   ሀ. የግል ☐

   ለ. ሽርክና ☐

   ሐ. የጋራ ማሕበር ☐

   መ.የመንግስት ☐

5. ድርጅቱ የሚያመርታቸው የምርት ዓይነቶች

   ሀ. ........................................ የታሪፍ ቁጥር ....................
   ለ. ........................................ የታሪፍ ቁጥር ....................
   ሐ. ........................................የታሪፍ ቁጥር ....................
   መ. ........................................የታሪፍ ቁጥር ....................

የድርጅቱ ባለቤት ስም..........................................................................

ፊርማ..........................................................................................

ማህተም

## ቅጽ ሦስት /ሀ/

## ያለፉት ሁለት የምርት ዓመታት የምርትና የሽያጭ አፈጻጸም/ለነባር አምራቾች/

| ተ.ቁ. | የተመረተ ምርት ዓይነት | የታሪፍ ቁጥር | መለኪያ | የተመረተ ምርት መጠን | የተሸጠ ምርት መጠን በብር | መግለጫ |
|---|---|---|---|---|---|---|
| | | | | | | |
| | | | | | | |
| | | | | | | |
| | | | | | | |
| | | | | | | |
| | | | | | | |
| | | | | | | |
| | | | | | | |
| | | | | | | |
| | | | | | | |
| | | | | | | |
| | | | | | | |
| | | | | | | |
| | | | | | | |
| | | | | | | |
| | | | | | | |
| | ድምር | | | | | |

የድርጅቱ ስም ........................................................ ፊርማ .................................... ማህተም

ቅጽ ሦስት /ለ/

በቅጽ ሦስት /ሀ/ የተዘረዘሩትን የምርት ዓይነቶች ለማምረት ጥቅም ላይ የዋለ ግብዓት መጠን በምርት ዓይነት

የምርት ዓይነት............................................የታሪፍ ቁጥር ..........................................................

| ተ.ቁ. | ጥቅም ላይ የዋለ የግብዓት ዓይነት | የታሪፍ ቁጥር | መለኪያ | መጠን | ብክነት በመቶኛ | መግለጫ |
|---|---|---|---|---|---|---|
| | | | | | | |
| | | | | | | |
| | | | | | | |
| | | | | | | |
| | | | | | | |
| | | | | | | |
| | | | | | | |
| | | | | | | |
| | | | | | | |
| | | | | | | |
| | | | | | | |
| | | | | | | |
| | | | | | | |
| | | | | | | |
| | | | | | | |
| | | | | | | |
| | ድምር | | | | | |

የድርጅቱ ስም.......................................... ፊርማ.............................. ማህተም

ቅጽ አራት/ሀ/

በምርት ዘመኑ የድርጅቱ የማምረት አቅምና የምርት ዕቅድ

| ተ.ቁ. | የምርት ዓይነት | የታሪፍ ቁጥር | መለኪያ | የማምረት አቅም | የምርት ዕቅድ | መግለጫ |
| --- | --- | --- | --- | --- | --- | --- |
| | | | | | | |
| | | | | | | |
| | | | | | | |
| | | | | | | |
| | | | | | | |
| | | | | | | |
| | | | | | | |
| | | | | | | |
| | | | | | | |
| | | | | | | |
| | | | | | | |
| | | | | | | |
| | | | | | | |

የድርጅቱ ስም ........................................................ ፊርማ .................................. ማህተም

ማሳሰቢያ ፡ በማምረት አቅምና በምርት ዕቅድ መካከል ልዩነት ካለ የልዩነቱ ምክንያት መግለጽ አለበት፡፡

## ቅጽ አራት/ለ/

በቅጽ አራት/ሀ/ ላይ በቀረበው የምርት ዕቅድ ላይ ተመሰረተ የግብዓት ፍላጎት ዕቅድ በምርት

የምርት ዓይነትና የታሪፍ ቁጥር.....................................................

| ተ.ቁ. | የግብዓት ዓይነት | የታሪፍ ቁጥር | መለኪያ | ከሀገር ውስጥ | ከውጪ | ጠቅላላ ፍላጎት | የግብዓት/ ምርት ጥመርታ |
|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | | | | | | | |
| | | | | | | | |
| | | | | | | | |
| | | | | | | | |
| | | | | | | | |
| | | | | | | | |
| | | | | | | | |
| | | | | | | | |
| | | | | | | | |
| | | | | | | | |
| | | | | | | | |
| | | | | | | | |
| | | | | | | | |
| | ድምር | | | | | | |

የድርጅቱ ስም............................................ ፊርማ.............................. ማህተም

# ቅጽ አምስት

## የጉምሩክ ታሪፍ ሁለተኛ መደብ /ሀ/ ተጠቃሚነት የምስክር ወረቀት ለማሳደስ የቀረበ ማመልከቻ

እኔ.......................................................በምስክር ወረቀት ቁጥር................ በ............. ቀን የተሰጠኝ የጉምሩክ ታሪፍ ሁለተኛ መደብ /ሀ/ ተጠቃሚነት የምስክር ወረቀት ባለበት ሁኔታ* ለሚቀጥለው የምርት ዘመን እንዲታደስልኝ እጠይቃለሁ፡፡

የአመልካች ስም.........................................................

የድርጅቱ ስም.........................................................

የግብር ከፋይ መለያ ቁጥር..............................................

ማመልከቻ የቀረበበት ቀን ..............................................

የአባሪ ገጽ ብዛት .......................................................

ፊርማ........................................................................

የድርጅቱ ማህተም.......................................................

*ባለበት ሁኔታ ማለት ለአሁኑ የምርት ዘመን የተፈቀደው የምርት ዕቅድ፣ የግብዓት ፍላጎት፣ የግብዓት / ምርት ጥመርታ እና የብክነት መጠን ለሚቀጥለው የምርት ዘመን ለውጥ የማይደረግበት ሲሆን ነው፡፡

# ቅጽ ስድስት

## የጉምሩክ ታሪፍ ሁለተኛ መደብ (ሀ) ተጠቃሚነት የምስክር ወረቀት ለማሻሻል የቀረበ ማመልከቻ

እኔ..........................................................በምስክር ወረቀት ቁጥር................ በ............. ቀን በተሰጠኝ መብት መሰረት የጉምሩክ ታሪፍ ሁለተኛ መደብ (ሀ) ተጠቃሚ ስሆን፣ በዚህ መመሪያ አንቀጽ ........ መሠረት የተጠቃሚነት የምስክር ወረቀቱ እንዲሻሻልልኝ አመለክታለሁ፡፡

የአመልካች ስም..........................................................

የድርጅቱ ስም..............................................................

የግብር ከፋይ መለያ ቁጥር ................................................

ማመልከቻ የቀረበበት ቀን ..................................................

የአባሪ ገጽ ብዛት ..........................................................

ፊርማ.......................................................................

የድርጅቱ ማህተም.........................................................

*ማሻሻያው የቀረበው የምስክር ወረቀቱ በሚታደስበት ጊዜ ከሆነ በዚህ ማመልከቻ መሰረት እንዲታደስና እንደተሻሻለ ይቆጠራል፡፡



የገንዘብና የኢኮኖሚ ትብብር ሚኒስቴር

## ቅጽ ሰባት/ሀ/

## በአምራች ድርጅት የሚዘጋጅ በምርት ዘመኑ የገባ የግብዓት መጠንና ዓይነት ሪፖርት*

የድርጅቱ ስም.......................................................................................

የግብር ከፋይ መለያ ቁጥር .............................................................................

የጉምሩክ ታሪፍ ሁለተኛ መደብ (ሀ) ተጠቃሚነት የምስክር ወረቀት ቁጥር........................

የምርት ዘመን ከ...........................................እስከ ...............................................

አድራሻ፡- ክልል.......................................ከተማ.............................ክፍለ ከተማ.................ወረዳ..............

ስልክ........................................ፋክስ...................................

| ተ.ቁ. | የግብዓት ዓይነት | የታሪፍ ቁጥር | መለኪያ | መጠን | ዕቃው የገባበት የጉምሩክ ጣቢያ | የዲክላራሲዮን ቁጥር |
|---|---|---|---|---|---|---|
| | | | | | | |
| | | | | | | |
| | | | | | | |
| | | | | | | |
| | | | | | | |
| | | | | | | |
| | | | | | | |

*ሪፖርቱ የሚቀርበው ለኢንዱስትሪ ሚኒስቴርና ለኢትዮጵያ ገቢዎችና ጉምሩክ ባለሥልጣን ነው፡፡

## ቅጽ ሰባት /ለ/

## የጉምሩክ ታሪፍ ሁለተኛ መደብ (ሀ) በመጠቀም ወደ ሀገር ውስጥ የገቡ ግብዓቶችን በመጠቀም በምርት ዘመኑ የተመረተ የምርት መጠን ሪፖርት

የግብዓት ዓይነት.......................................................የታሪፍ ቁጥር................................ መጠን...............................

| ተ.ቁ. | የተመረተ ምርት ዓይነት | የታሪፍ ቁጥር | መለኪያ | መጠን | የግብዓት /ምርት ጥመርታ | የግብዓት ብክነት | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | | | | | | በመጠን | በመቶኛ |
| | | | | | | | |
| | | | | | | | |
| | | | | | | | |
| | | | | | | | |
| | | | | | | | |
| | | | | | | | |
| | | | | | | | |

የደርጅቱ ባለቤት ስም...................................................
ፊርማ..................................ማህተም...........................

*ይህ ሪፖርት የምርት ዘመኑ እንዳበቃ ቀጥሎ ባሉት 30 የሥራ ቀናት ውስጥ ለኢንዱስትሪ ሚኒስቴርና ለገቢዎችና ጉምሩክ ባለስልጣን መቅረብ አለበት

# ቅጽ ስምንት

## የጉምሩክ ታሪፍ ሁለተኛ መደብ (ሀ) አጠቃቀም አመታዊ ሪፖርት

1. የድርጅቱ ስም.................................................................................................
2. የግብር ከፋይ መለያ ቁጥር..........................................................................
3. የሁለተኛ መደብ /ሀ/ የምስክር ወረቀት ቁጥር ...........................................................
4. በገቢዎችና ጉምሩክ ባለስልጣን ሪፖርቱን ያዘጋጀው የስራ ክፍል..................................
   4.1. ያዘጋጀው ሠራተኛ ሙሉስም..............................................................
   4.2. የሥራ ድርሻ ..........................................................................................
   4.3. ቀን..................................ፊርማ.....................................................
   4.4. ያጸደቀው ሀላፊ ሙሉ ሥም ስም........................................................
   4.5. የሥራ ድርሻ ..........................................................................................
   4.6. ቀን..................................ፊርማ.....................................................
5. የግብዓቱ ዓይነት .....................................................
6. የግብዓቱ የታሪፍ ቁጥር ..........................................
7. በምርት ዘመኑ ግብዓቱ ወደ ሀገር ውስጥ የገባበት ዲክላራሲዮን ቁጥር.........................
8. በምርት ዘመኑ ግብዓቱ ወደ ሀገር ውስጥ የገባበት ቀን ..........................................
9. ግብዓቱን በመጠቀም የተመረተ ምርት ዓይነት.......................................................
10. ግብዓቱን በመጠቀም የተመረተ ምርት የታሪፍ ቁጥር..............................................
11. የተፈቀደው የግብዓት ምርት ጥመርታ ..........................................................
12. የተፈቀደው የብክነት መጠን በመቶኛ..........................................................

# የጉምሩክ ታሪፍ ሁለተኛ መደብ (ሀ) ተጠቃሚነት የምስክር ወረቀት

የፍቃድ ቁጥር.........................................

የተሰጠበት ቀን.........................................

የድርጅቱ ስም .........................................

የተሰማራበት የማምረት ዘርፍ .......................

የግብር ከፋይ መለያ ቁጥር ..........................

የካፒታል መጠን.........................................

አድራሻ፡ ክልል..........................ከተማ................ክፍለ ከተማ ...............ስልክ...............

የኢንዱስትሪ ሚኒስቴር የጉምሩክ ታሪፍ ሁለተኛ መደብ (ሀ) ተጠቃሚ ለሆኑ አምራች ድርጅቶች በመመሪያ ቁጥር .........................አንቀጽ...................... በተመለከተው መሠረት በቁጥር ......በቀን................. የቀረበው የሁለተኛ መደብ (ሀ) ተጠቃሚነት ማመልከቻ ተቀባይነት ስላገኘ ይህን የምስክር ወረቀት ሰጥቷል፡፡

ድርጅቱ በምርት ዘመኑ የሚያመርተው የምርት ዓይነትና መጠን

| ተ.ቁ. | የምርት ዓይነት | የታሪፍ ቁጥር | መለኪያ | መጠን |
|---|---|---|---|---|
| | | | | |
| | | | | |
| | | | | |
| | | | | |

በምርት ዘመኑ የድርጅቱ የግብዓት አጠቃቀም

| ተ.ቁ. | የግብዓት ዓይነት | የታሪፍ ቁጥር | መለኪያ | የግብዓት ምርት ጥመርታ | የብክነት መጠን |
|---|---|---|---|---|---|
| | | | | | |
| | | | | | |
| | | | | | |
| | | | | | |

የፍቃድ ሰጪው ኃላፊ ፊርማ ....................................... ማህተም

## ሠንጠረዥ 1፡-

## በየኢንዱስትሪ ንዑስ ዘርፍ ሊታከል የሚገባ የተጨማሪ እሴት መጣኔ

| የኢንዱስትሪ ንዑስ ዘርፍ | የተጨማሪ እሴት መጣኔ (%) |
|---|---|
| 1. MANUFACTURE OF FOOD PRODUCTS AND BEVERAGES | |
| 1.1. Production, processing and preserving of meat, fruit and vegetables | 11 |
| 1.2. Manufacture of vegetable and animal oils and fats. | 24 |
| 1.3. Manufacture of dairy products | 12 |
| 1.4. Manufacture of grain mill products | 24 |
| 1.5. Manufacture of processed honey and wax | 24 |
| 1.6. Manufacture of prepared animal feeds | 25 |
| 1.7. Manufacture of bakery products | 28 |
| 1.8. Manufacture of sugar and sugar confectionery | 30 |
| 1.9. Manufacture of macaroni and spaghetti | 30 |
| 1.10. Manufacture of food products n.e.c. | 27 |
| 1.11. Distilling, rectifying and blending of spirits | 26 |
| 1.12. Manufacture of wines | 41 |
| 1.13. Manufacture of malt liquors and malt | 24 |
| 1.14. Manufacture of soft drinks & production of mineral waters | 21 |
| 2. MANUFACTURE OF TOBACCO PRODUCTS | |

| የኢንዱስትሪ ንዑስ ዘርፍ | የተጨማሪ እሴት መጣኔ (%) |
|---|---|
| 2.1. Manufacture of tobacco products | 32 |
| 3. MANUFACTURE OF TEXTILES | |
| 3.1. Spinning, weaving and finishing of textiles | 15 |
| 3.2. Manufacture of cordage, rope, twine and netting | 21 |
| 3.3. Knitting mills | 19 |
| 4. MANUFACTURE OF WEARING APPAREL, EXCEPT FUR APPAREL | |
| 4.1. Manufacture of wearing apparel except fur apparel. | 22 |
| 5. TANNING AND DRESSING OF LEATHER; MANUFACTURE OF FOOTWEAR, LUGGAGE AND HANDBAGS | |
| 5.1. Tanning and dressing of leather,luggage and handbags | 23 |
| 5.2. Manufacture of footwear. | 21 |
| 6. MANUFACTURE OF WOOD AND OF PRODUCTS OF WOOD AND CORK, EXCEPT FURNITURE | |
| 6.1. Manufacture of wood and of products of wood and cork, except furniture | 13 |
| 7. MANUFACTURE OF PAPER, PAPER PRODUCTS AND PRINTING | |
| 7.1. Manufacture of paper and paper products. | 27 |
| 7.2. Publishing and printing services. | 31 |
| 8. MANUFACTURE OF CHEMICALS AND CHEMICAL PRODUCTS | |
| 8.1. Manufacture of basic chemicals, except fertilizers and nitrogen compounds. | 25 |
| 8.2. Manufacture of paints, varnishes and mastics . | 26 |

| የኢንዱስትሪ ንዑስ ዘርፍ | የተጨማሪ እሴት መጣኔ (%) |
|---|---|
| 8.3. Manufacture of pharmaceuticals, medicinal chemicals and botanical products | 26 |
| 8.4. Manufacture of soap and detergents cleaning and polishing, perfumes and toilet preparations. | 26 |
| 8.5. Alkeyd Resin | 23 |
| 8.6. Pesticides | 18 |
| 8.7. Manufacture of chemical products n.e.c. | 26 |
| 9. MANUFACTURE OF RUBBER AND PLASTIC PROCDUCTS. | |
| 9.1. Manufacture of rubber products.. | 21 |
| 9.2. Manufacture of plastic products. | 24 |
| 10. MANUFACTURE OF OTHER NON-METALLIC MINERAL PRODUCTS | |
| 10.1. Manufacture of glass and glass products. | 35 |
| 10.1. Manufacture of structural clay products | 36 |
| 10.2. Manufacture of cement, lime and plaster . | 40 |
| 10.3. Manufacture of articles of concrete, cement and plaster | 31 |
| 10.4. Manufacture of non-metallic mineral products n.e.c.. | 38 |
| 11. MANUFACTURE OF BASIC METALS | |
| 11.1. Manufacture of basic iron and steel | 10 |
| 11.2. Manufacture of basic precious and non-ferrous metals | 10 |
| 11.3. Casting metals | 10 |
| 11.3.1. Casting of iron and steel | 10 |

| የኢንዱስትሪ ንዑስ ዘርፍ | የተጨማሪ እሴት መጣኔ (%) |
|---|---|
| 11.3.2. Casting of non-ferrous metals | 10 |
| 12. MANUFACTURE OF FABRICATED METAL PRODUCTS, EXCEPT MACHINERY AND EQUIPMENT | |
| 12.1. Manufacture of structural metal products, tanks, reservoirs and containers of metal . | |
| 12.1.1. Manufacture of structural metal products | 15 |
| 12.1.2. Manufacture of thanks, reservoirs, and container of metal | 15 |
| 12.1.3. Manufacture of steam generators, except central heating hot water boilers | 15 |
| 12.2. Manufacture of other fabricated metal products; metal working service activities | 12 |
| 12.2.1. Forging, pressing, stamping and roll-forming of metal; powder metallergy | 12 |
| 12.2.2. Tretment and coating of metals; machining | 12 |
| 12.3. Manufacture of cutlery, hand tools and general hardware . | 12 |
| 12.3. Manufacture of other fabricated metal products . | 12 |
| 13. MANUFACTURE OF MACHINERY AND EQUIPMENT | |
| 13.1. Manufacture of general-purpose machinery | 15 |
| 13.1.1. Manufacturing of engines and turbines, except aircraft, vehicle and cycle engines | 15 |
| 13.1.2. Manufacture of fluid power equipment | 15 |

| የኢንዱስትሪ ንዑስ ዘርፍ | የተጨማሪ እሴት መጣኔ (%) |
|---|---|
| 13.1.3. Manufacture of other pumps, compressors, taps and valves | 15 |
| 13.1.4. Manufacture of bearings, gears, gearing and driving elements | 15 |
| 13.1.5. . Manufacture of ovens, furnaces and furnace burners | 15 |
| 13.1.6. Manufacture of lifting and handling equipment | 15 |
| 13.1.7. Manufacture of office machinery and equipment (except computers and peripheral equipment) | 15 |
| 13.1.8. Manufacture of power-driven hand tools | 15 |
| 13.1.9. Manufacture of other general purpose machinary | 15 |
| 13.2. Manufacture of special- purpose machinary | 15 |
| 13.2.1. Manufacture of agricultural and forestry machinery | 15 |
| 13.2.2. Manufacture of metal-forming machinery and machine tools | 15 |
| 13.2.3. Manufacture of machinery for metallergy | 15 |
| 13.2.4. Manufacture of machinery for mining, quarrying and construction | 15 |
| 13.2.5. Manufacture of machinery for food, beverage and tobacco processing | 15 |
| 13.2.6. Manufacture of machinery for textile apparel and leather production | 15 |
| 13.2.7. Manufacture of other special-purpose machinery | 15 |
| 14. MANUFACTURE OF MOTOR VEHICLES,TRAILERS | |



Ethiopian ... Records & Documentation ...

| የኢንዱስትሪ ንዑስ ዘርፍ | የተጨማሪ እሴት መጣኔ (%) |
|---|---|
| & SEMI-TRAILERS | |
| 14.1. Manufacture of motor vehicles. | 10 |
| 14.2. Manufacture of bodies (coach work) for motor vehicles; manufacture of trailers and semi trailers | 15 |
| 14.3. Manufacture of parts and accessaries for motor vehicles | 15 |
| 15. MANUFACTURE OF OTHER TRANSPORT EQUIPMENT | |
| 15.1. Building of ships and boats | 15 |
| 15.1.1. Building of ships and floating structures | 15 |
| 15.1.2. Building of pleasue and sporting boats | 15 |
| 15.2. Manufacture of raiway locomotives and rolling stock | 15 |
| 15.3. Manufacture of air and spacecraft and related machinery | 15 |
| 15.4. Manufacture of military fighting vehicle | 15 |
| 15.5. Manufacture of transport equipment | 15 |
| 15.5.1. Manufacture of mororcycles | 15 |
| 15.5.2. Manufacture of bicycles and invalid carriages | 15 |
| 15.5.3. Manufacture of other transport equipment | 15 |
| 16. MANUFACTURE OF FURNITURE | |
| 16.1. Manufacture of furniture | 15 |
| 17. OTHER MANUFACTURING | |
| 17.1. Manufacture of jewellery, bijouterie and related article | 15 |
| 17.1.1. Manufacture of jewellery and related articles | 15 |
| 17.1.2. Manufacture of imitation jewellery and related articles | 15 |

| የኢንዱስትሪ ንዑስ ዘርፍ | የተጨማሪ እሴት መጠን (%) |
|---|---|
| 17.2. Manufacture of musical instruments | 15 |
| 17.3. Manufacture of sports goods | 15 |
| 17.4. Manufacture of games and toys | 15 |
| 17.5. Manufacture of medical and dental instruments and supplies | 10 |
| 17.6. Other manufacturing | 15 |
| 18. REPAIRS AND INSTALLATION OF MACHINERY AND EQUIPMENT | |
| 18.1. Repair of fabricated metal products, machinery and equipment | 10 |
| 18.1.1. Repair of fabricated metal products | 10 |
| 18.1.2. Repair of machinery | 10 |
| 18.2. Repair of electronic and optical equipment | 5 |
| 18.3. Repair of electrical equipment | 5 |
| 18.4. Repair of transport equipment except, motor vehicle | 10 |
| 18.5. Repair of other equipment | 10 |
| 18.6. Instalation of industrial machinery and equipment | 5 |
| 19. MANUFACTURE OF COMPUTER, ELECTRONIC AND OPTICAL PRODUCTS | |
| 19.1. Manufacture of electronic components and boards | 5 |
| 19.2. Manufacture of computers, TVs and peripheral equipment | 7 |
| 19.3. Manufacture of communication equipment including mobile phone | 5 |
| 19.4. Manufacture of consumer electronics | 5 |

| የኢንዱስትሪ ንዑስ ዘርፍ | የተጨማሪ እሴት መጠን (%) |
|---|---|
| 19.5. Manufacturing of measuring, testing, navigating and control equipment; watches and clocks | 5 |
| 19.5.1. Manufacturing of measuring, testing, navigating and control equipment | 5 |
| 19.5.2. Manufacture of watches and clocks | 5 |
| 19.6. Manufacture of irradiation, electro medical and electrotherapic equipment | 5 |
| 19.7. Manufacture of optical instruments and photographic equipment | 5 |
| 19.8. Manufacture of magnetic and optical media | 5 |
| 20. MANUFACTURE OF ELECTRICAL EQUIPMENT | |
| 20.1. Manufacture of electric motors, generators, transformers and electricity distribution and control apparatus | 10 |
| 20.2. Manufacture of batteries and accumulators | 15 |
| 20.3. Manufacture of wiring and wiring devices | 10 |
| 20.3.1. Manufacture of fiber optic cables | 10 |
| 20.3.2. Manufacture of other electronic and electric wires and cables | 10 |
| 20.3.3. Manufacrure of wiring device | 10 |
| 20.4. Manufacture of electric lighting equipment | 10 |
| 20.5. Manufacrure of domestic appliances | 10 |
| 20.6. Manufacture of other electrical equipment | 10 |